# ፀረ-አማራነትን ለመፋረድና የሚታሰበውንም

# አደጋ በእንጭጩ ለመቅጨት እንደ ሳይመን ቪዚንቶል

# ማዕከል ዓይነት ዘረኛ ወንጀለኞችን አዳኝና አንቆ ለፍርድ አቅራቢ

# ድርጅት መቋቋም አለበት

ከአስተዋይ በቀለ

አማራ፣ የወያኔ የክልል ካርታ እንደሚያሳየውና የቄብሳይቶች የተሳሳቱና አሳሳች መረጃዎች እንደሚያስነብቡት ሳይሆን፤ በሕዝብ ብዛቱ፣ በቆዳ ስፋቱ፣ በአሰፋፈሩ መላ-ኢትዮጵያን ያዳረሰ፣ ከሁሉም ብሔረሰቦች ጋር ተዋልዶ የተሳሰረና ሥር የሰደደ ትልቅና ግዙፍ ነው፡፡

ይህ የኢትዮጵያ ሕዝብ ክፍል አርቆ አስተዋይና ታጋሽ ኃይል ከመሆኑ ጋር ኢትዮጵያን፣ ኢትዮጵያዊነትንና ሰንደቅ ዓላማን መለዮና እምነት አድርጎ በፅኑ የቆመ ፣ የማይበርድ፣ የማይበገር፣ እጅ የማይሰጥ አሸናፊና ወሳኝ ነው።

አማራ እግዚአብሔርን የሚፈራ፣ ቸርነቱንና ደግነቱን ያስተዋለ፣ ልቦናው ንፁህ የሆነ፣ መንፈሳዊ ፀጋን የተላበሰ፣ አብሮ በሰላም መኖርን፣ ፍትህን፣ እኩልነትን፣ መከባበርን፣ የጋራ እድገትን፣ ብሔራዊ ብልፅግናን፣ የሕግ የበላይነትንና ዴሞክራሲን ያነገበ ፣ ለዘመናት በብሔራዊ ታሪኩና ነፃነቱ የሚኮራ፣ ደስታና መከራን ከሌላው ጋር እኩል ተካፍሎ የሚኖር ሠላማዊ ሕዝብ ነው።

በዚህ ገርና ሠላማዊ ሕዝብ ላይ በየግዜውና በየቦታው ዓይነ -ሕሊናቸው የጨለመና የላቀጠ አክራሪ የዘር ትዕቢተኞች በድርጅትና በመንግሥት ደረጃ እየተነሱ እጅግ አሰቃቂ ጀኖሳይድና ደሞሳይድ ፈጽመውበታል።

ኦነግ፣ ሻቢያ፣ ወያኔ፣ ደርግና መኢሶን የአማራውን ሕዝብ ንፁህ ደም ያፈሰሱ ወንጀለኞች ሲሆኑ፤ በተለይ ኦነግ ተብየው ከመነሻው አጀንዳው የተቀረጸው የአማራን ሕልውና ለማጥፋት ባቀደና ባለመ ጀኖሳይድ ፕሮግራም በመሆኑ ከሁሉም በላይ አማራውን በግፍ ፈጅቷል።

የኦነግ ወንጀለኞች፣ ተባባሪዎችና ደጋፊዎች በአማራው ላይ በፈፀሙት እልቂት ሳይሳቀቁና ሳይሸማቀቁ በአገር ውስጥና በዓለም ዙርያ እንደልባቸው ስለሚኖሩ እነዚህን ዘረኛ ፀረ-ሕዝብ ወንጀለኞች እየለቀሙና አሳዶ እያነቁ ለፍርድ ማቅረብ የማይቀር ተግባር ነው።

የሚፈለገው ፥ የጀኖሳይድና የደሞሳይድ ወንጀለኞች ፀፀትና ይቅርታ ሳይሆን እንደ ናዚና ሯዋንዳ ፋሽስት ወንጀለኞች ታድነው ለፍርድ መቅረብና ትክክለኛ ብያኔና ቅጣት እንዲያገኙ ማስደረግ ነው።

ናዚዎች በዘር ትዕቢት ተነሳስተው በአይሁዶች ላይ የፈጸሙባቸውን ከባድ እልቂት አይሁዶች ይሁን ደግ ብለው አልተውትም። እንደ እነ ሳይመን ቪዚንቶል ዓይነት ወንጀለኛ አዳኞችን ከመካከላቸው አፍርተው ቀንደኛ ናዚ የዘር ወንጀለኞችን ከተደበቁበት አድነው በመያዝ ለፍርድ አቅርበዋቸዋል።

አማራው ደግም ሌባና ነፍሰ ገዳይን ማደን ሕጋዊ ባሕል አድርጎት የቆየ የፍትህ አሰራር በመሆኑ እንደ እነ ሳይመን ቪዚንቶል ማዕከል ዓይነት ድርጅት መፍጠርና ጀኖሳይድና ደሞሳይድ የፈጸሙበትን ወንጀለኞች አድኖና አሳዶ ለፍርድ ማቅረብ አይሳነውም።

አማራው በአርቆ አስተዋይነቱና በታጋሽነቱ ያኘከውን በዓመቱ ነው የሚውጠው እንደተባለው ሆኖ ነው እንጂ፤ ከተቀሰቀሰና የእርስ- በርስ የግንኙነት መስመር ካደራ ቆይቷል። በሚፈጥረው የዘር ወንጀለኞች አደና ማዕከልና ባላሰለሰ ክትትሉ እልቂት የፈጸሙበትን እንደ ሚፋረዳቸው ጥርጥር የለውም ።

የጌታችን የእየሱስ ክርስቶስ መምጫና የአማራው ሕዝብ መነሻ ስዓት አይታወቅም እያሉ ራሳቸው በፈጠሩት ሥጋት በመሸበር አሁንም ዘረኞች ለአማራው እንዳልተኙ ይታያል ፣ ይሰማል ።

በግንቦት 7 ውስጥ የተኮለኮሉት ግለሰቦችና አጋር ድርጅቶች አሰላለፍና አያያዝ፣ የኢሳት ቴሌቪዥን ማሸንክ ቃለ- ምልልስና የለበጣ ፕሮፓጋንዳ፣ የመድረክ አላቢላዎች ሐኬት ሁሉ አካሄድ አማራውን በፖለቲካ ያገለለና ለሌላም የዘር እልቂት ለመዳረግ በስውር ያሴረ ፀረ- አማራነት፣ ፀረ- ኢትዮጵያ፣ ፀረ- ኢትዮጵያዊነትና ፀረ- ሰንደቅ ዓላማ ነው ።

አማራና ውቅያኖስ ቢጨልፉት- ቢጨልፉት የማያልቅ በሁሉም ኢትዮጵያዊ ደም ውስጥ ያለ ግዙፍ ኢትዮጵያና ኢትዮጵያዊነት ኃይል በመሆኑ ይህን ሕዝብ በፖለቲካ ማግለልና ለማጥፋትም ማሰብ በእያንዳንዳቸው ሱሪ ውስጥ በተጠመደ ፈንጂ እንደመጫወት ነው።

ፀረ- አማራነትን ለመፋረድ ፣ ለመከላከልና ኢትዮጵያን ለማዳን እያንዳንዱ ኢትዮጵያዊ ኃላፊነት ስላለበት ሁሉም ለኢትዮጵያ፣ ለኢትዮጵያዊነት፣ ለሰንደቅ ዓላማና ለሕግ የበላይነት ዘብ ይቁም ።

- በዘር ወንጀለኞች ላይ ማስረጃ ማሰባሰብና ክትትል ይፋፋም!
- ሕግና ፍትህ ያሸንፋል !!
- ምንጊዜም ኢትዮጵያ !!!